ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 49/11

ቀን: 20/05/2011 ዓ.ም

- ለ፡- ሁሉም ስራ ሂደቶች
- ከ፡- ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት

አ/አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አለማየሁ አንቲቾ ደዴቦ
ስራ አስኪያጅ
Alemayehu Anticho dedebo

ጉዳዩ፡- እቃ ሳይደርስ የዕቃ አወጣጥ አሰራር ተግባራዊ እንዲደረግ የተላከውን ይመለከታል፣

ከጉምሩክ ኮሚሽን በቁጥር 4.0/390/11 በቀን 17 ጥር 2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 28 በተደነገገው መሠረት ዕቃ ሳይደርስ የዕቃ አወጣጥ ስርዓት ለመፈጸም የአሠራር ስርዓት በቁጥር 3.0/642/09 በቀን 19 መጋቢት 2009 ዓ.ም የተላለፈው የአሰራር ስርዓት ላይ ማስተካከያ የተደረገ መሆኑን አሳውቆናል።

ስለዚህ ዕቃው ሳይደርስ የዕቃ አወጣጥ አሠራር ስርዓት 10 ገጽ ከኮሚሽኑ የተላከውን አያይዘን የላክን በመሆኑ በዚሁ መሠረት እንዲያውቁትና በጥንቃቄ እንዲፈጸም አሳስባለሁ።

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፡-

- ለአምራች ውጪ ዕቃና ሌሎች ጣቢያዎች ም/ስራ አስኪያጅ
- ለም/ሥራ አስኪያጅ /የንግድ ገቢ ዕቃዎች/
- ለህግ ህግ ተገዥነት ም/ስራ አስኪያጅ
  አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ገቢዎች ሚኒስቴር
የጉምሩክ ኮሚሽን

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues
Customs Commission


ቀን 7 ጥር 201
Date
ቁጥር 4.0/390/11
Ref. No.

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች

በያሉበት

ጉዳዩ፡- **ዕቃ ሳይደርስ የዕቃ አወጣጥ አሰራር ተግባራዊ እንዲደረግ ስለማሳወቅ**

በጉምሩክ አዋጅ 859/06 አንቀጽ 28 በተደነገገው መሠረት ዕቃ ሳይደርስ የዕቃ አወጣጥ ስርዓት ለመፈፀም የአሠራር ስርዓት ተዘጋጅቶ በቁጥር 3.0/642/09 በቀን 19/መጋቢት/2009 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲደረግ የተላከ መሆኑ የታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት የተላለፈው አሠራር ላይ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት አሠራሩ በአዲስ መልክ ተዘጋጅቷል፡፡

ስለሆነም ዕቃ ሳይደርስ የዕቃ አወጣጥ አሠራር ስርዓት 10 ገጽ አያይዘን የላክን ስለሆነ በዚሁ መሠረት በጥንቃቄ እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አንዘነው ጫኔ አበበ
የጉምሩክ ኦፕሬሽን
ዘርፍ ም/ኮሚሽነር

ግልባጭ

- ለገቢዎች ሚኒስቴር ጽ/ቤት
  **ገቢዎች ሚኒስቴር**
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
- ለዕቃ አወጣጥ አሰራር ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍና የስሪት አገር ዳይሬክቶሬት
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
  **ጉምሩክ ኮሚሽን**

20/05/11

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!!


+251 116 62 98 00 +251 116 62 98 48
+251 116 62 98 19
2559
Addis Ababa, Ethiopia

# ዕቃ ሳይደርስ የእቃ አወጣጥ ሥርአት (pre-arrival clearance) አገልግሎት ለማስጀመር የተዘጋጀ ሰነድ

Ethiopian Customs Commission
Record & Documentation

# ዕቃ ሳይደርስ የእቃ አወጣጥ ሥርአት
# (Pre-arrival clearance)
# ለማስጀመር የተዘጋጀ ሰነድ

## 1. መግቢያ

ዕቃ ሳደርስ የዕቃ አወጣጥ ስርዓት (pre-arrival clearance)የጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥ እና የቁጥጥር ሥርዓቱ ሚዛኑን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ዓይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀፅ 28 እንዲሁም የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈፃፀም ማንዋል ላይ ስርዓቱ ተፈፃሚ እንዲደረግ ተካቷል፡፡ይህየዕቃ አወጣጥ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ ንግድናኢንቨስትመንቱ ላይ የሚስተዋለውን ተጨማሪ ወጪና የጊዜ ብክነት የሚቀንስ ከመሆኑ ባለፈ የእቃዎችን የወደብ ላይ ቆይታ በማሳጠር የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

ስለሆነም ሥርዓቱ በተሟላ አግባብ መፈፀም የሚያስችል አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ ከዚህ በታች በተቀመጠው መሰረት የእቃ አወጣጥ ስርአት መፈፀም(pre-arrival clearance) ለመተግበር የሚያስችል አሰራር ተቀርፃል፡፡

## 2. ዕቃ ሳይደረስ የዕቃ አወጣጥ ስርአት መፈፀም /pre- arrival clearance/

ዕቃሳይደረስ የዕቃ አወጣጥ ሥርዓት መፈፀም (pre- arrival clearance) ማለት አስመጪው ወይም ወኪሉ ዕቃው ከመድረሱ ወይም ትራንዚት ከማጠናቀቁ በፊት በሚያቀርቡት የእቃዲክለራሲዮን እና አባሪ ሰነዶች አስቀድመው እንዲያቀርቡና ሰነዱ እንዲመረመር በማድረግ በሰነዱ የስጋት ደረጃመሰረት እቃው እንደደረሰ ለነፃ ዝውውር መልቀቅየሚያስችል የዕቃ አወጣጥ ስርዓት ነው፡፡

### 2.1 ዕቃ ሳይደርስ የእቃ አወጣጥ ስርአት መፈፀም (pre- arrival clearance) የሚያስገኘውጠቀሜታ

#### 2.1.1 ለአስመጪ

- የሰነድ ምርመራ ስራ ዕቃ ከመድረሱ አስቀድሞ የሚከናወን ስለሆነ የዕቃዎች የወደብና መጋዘን ቆይታ ጊዜ ያሳጥራል፤
- የመጋዘን እና የዲሜሬጅ ወጪ በመቀነስ አስመጪውን አላስፈላጊ ከሆኑ ወጭዎች ይታደጋል፡፡



Ethiopian Customs Commission Record & Documentation

- በዚህ ስርዓት መስተናገድ አስመጪው ያስመጣቸውን ዕቃዎች በፍጥነት ለገበያ ለማቅረብ ዕድል ይሰጣል፤

### 2.1.2 ለባንኮች

- በLC እና CAD ወደ አገር ለሚገቡ ዕቃዎች አስመጪው ሰነድ ለመረከብ ክፍያውን ለባንክ ወዲያውኑ መፈፀም ስለሚጠበቅበት የባንኮችን ስራ የተቀላጠፈ እንዲሆን ያደርጋል፤

### 2.1.3 ለባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት

- ደረቅ ወደቦች ላይ የሚፈጠረውን ክምችት ይቀንሳል፤
- የዕቃዎች የደረቅ ወደብ ቆይታ /Dwell time/ ይቀንሳል፤
- በውጭ ምንዛሬ የሚከፈለውን የኮንቴነር ዲመሬጅ ወጪ ይቀንሳል፤

### 2.1.4 ለጉምሩክ

- አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋና ፈጣን እንዲሆን ያደርጋል፤
- የሰው ሃይል አጠቃቀም ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፤
- የጉምሩክ መጋዘኖች አጠቃቀም ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፤
- ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚደረገውን የህግ ማስከበር ስራ ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፤
- የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ያግዛል፤

## 2.2 ዕቃ ሳይደርስ የእቃ አወጣጥ ስርአት (pre- arrival clearance)የተፈፃሚነት ወሰን

- እቃቸው ደረቅ ወደብ ከመድረሱ እናትራንዚት ከመጠናቀቁ በፊት አስፈላጊውን የሰነድ ዝግጅት በማድረግ እና ዲክለራሲዮን በመሙላት እንዲሁም ቀረጥና ታክስ በመክፈል ወይም የቀረጥ ነፃ ማስረጃ በማቅረብ ሰነድ ለጉምሩክ ማስገባት የሚችል ወይም ፈቃደኛ የሆኑ ሁሉም አስመጪዎች የትኛውም አይነት ዕቃ በpre- arrival clearance ስርዓት በመጠቀም የማስገባትመብት ይኖራቸዋል፡፡



[stamp]


## 3. ዕቃ ከመድረሱ በፊት የሚፈፀም የዕቃ አወጣጥ ስርአት (pre- arrivalclearance)የስራ ሂደት ፍሰት የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ

### 3.1 የመጀመሪያ ደረጃ ተግባር

#### 3.1.1 ሰነድ ለጉምሩክ ማስገባት እና ተቀባይነት ማግኘት

በአስመጪው ወይም በወኪሉ በኩል እቃው ከመድረሱ ወይም ትራንዚት ከማጠናቀቀ በፊት ዲክለራሲዮን መመዝገብ ፣የቀረጥና ታክስ ልኩን በማስላትና ክፍያ በመፈፀም ወይም የቀረጥ ነፃ ማስረጃ በማስያዝየጉምሩክ ዲክለራሲዮን እና በአዋጅ 859/2006 አንቀጽ 10 የተዘረዘሩለጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈፃፀም አስፈላጊ ከሆኑ ሰነዶች ጋር በማያያዝ በአካል ለጉምሩክ በማቅረብ ተቀባይነት ማግኘት ፡፡

#### 3.1.2ስዕላዊ መግለጫ



### 3.1.3 <u>ፈፃሚ አካል</u>


**የጉምሩክ አስተላላፊ**

### 3.2 ሁለተኛ ደረጃ ተግባር

#### 3.2.1 ሰነድ መረከብ እና ተቀባይነት መስጠት

- በአስመጪው ወይም በወኪሉ በኩል አባሪ ዲክለራዮን እና ደጋፊ ሰነዶች ሲቀርቡ በ ፌዝቬትቼክ ሊስት መሰረት የተሞሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ በሲስተም ተቀባይነት (acceptance)መስጠት እና የስጋት ደረጃውን በሲስተም በመወሰን ለቀጣይ ስራ ማስተላለፍ

#### 3.2.2 ስእላዊ መግለጫ




ፈፃሚ አካል፡- የሰነድ መረካከቢያና ማረጋገጫ ኦፊሰር

## 3.3 ሦስት ደረጃ ተግባር

### 3.2.1 የሰነድ ምርመራ ስራ ማከናወን

የቀረቡ ሰነዶች ተገቢውን ቀረጥና ታክስ የተከፈለባቸው ስለመሆኑ ወይም የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው መሆኑን በሰነዱ የስጋት ደረጃ መሰረት የተሟላ የሰነድ ምርመራ ስራ በማከናወን ማረጋገጥ ፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

### 3.3.2 ለአረንጓዴ (green) የስጋት ደረጃ

- ከአስመጪው ወይም ወኪሉ በአካል የቀረቡ ሰነዶች የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- ከተቆጣጣሪ መ/ቤት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ፈቃዱ እንዲቀርብ ማድረግ
- እቃው ትራንዚት አጠናቆ $T_1$Validate መደረጉን ማረጋገጥ እና ትራንዚት የተጠናቀቀበትን መንገድ ወረቀቱ እንዲቀረብ ማድረግ
- መልቀቂያ መስጠት
- ሙጨረሻ

ፈፃሚ አካል፡- የሰነድ መረካከቢያና ማረጋገጫ ኦፊሰር

### 3.3.3 ለቢጫ (yellow) የስጋት ደረጃ

- ከፌዝ ሼት ኦፊሰርሰነድ መረከብ
- ከዋጋ፣ ከታሪፍ፣ ከCPC ፣ በስሪት ሀገር አንፃር የተሟላ የሰነድ ምርመራ ማከናወን እና ተገቢ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን ወይም የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤
- የተከፈለው ቀረጥና ታክስ አንሶ የተገኘ ከሆነ ዕቃ እስኪደርስ መጠበቅ ሳያስፈልግ ተጨማሪውን ቀረጥና ታክስ ማስከፈል፤
- የቀረበው ሰነድ ለዋጋ አተማመን እና ለታሪፍ አመዳደብ መሟላት ያለባቸውን መረጃዎች ያላሟላ ከሆነ የሰነዱን የስጋት ደረጃ ተቀይሮ በፍተሻ ተረጋግጦ እንዲቀርብ ማድረግ፤
- ከተቆጣጣሪ መ/ቤት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ፈቃድ እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

- እቃው ትራንዚት አጠናቆ $T_1$Validate መደረጉን ከsystem ማረጋገጥ እና ትራንዚት የተጠናቀቀበት መንገድ ወረቀት እንዲቀርብ ማድረግ፡፡
- የእቃመልቀቂያ መስጠት

**ፈፃሚ አካል፡- የሰነድ ምርመራ ኦፊሰር**

### 3.3.4 ለቀይ (Red) የስጋት ደረጃ

- ከሰነድ መረካከቢያና ማረጋገጫ ኦፊሰር ሰነድ መረከብ
- ከዋጋ፣ከታሪፍ፣ከCPC፣ ከስሪት ሀገር አንፃር የተሟላ የሰነድ ምርመራ ማከናወን እና ተገቢ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን ማረጋገጥ ወይም የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፡፡
- የተከፈለው ቀረጥና ታክስ አንሶ የተገኘ ከሆነ ዕቃ እስኪደርስ መጠበቅ ሳያስፈልግ ተጨማሪውን ቀረጥና ታክስ ማስከፈል፣
- የሰነድ ምርመራ ስራው ከተጠናቀቀ በኃላ ሰነዱን ለፍተሻ ኦፊሰር ማስተላለፍ እንዲሁም ለዋጋ ትመና ታሪፍ አመዳደብ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ እንዲቀረቡ ለይቶ ለፍተሻ ኦፊሰሩ መግለፅ
- የፍተሻ ሪፖርቱ ልዩነት የሌለው ከሆነ ትራንዚት መጠናቀቅ እና$T_1$Validate መደረጉን በማረጋገጥ እንዲሁም የተቆጣጣሪ መ/ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው ከሆነ እንዲያቀርቡ በማድረግ መልቀቂያ መስጠት
- የፍተሻ ውጤቱ የልዩነት ሪፖርት የቀረበበት ከሆነ በመመሪያ 112/2008 መሰራት በአስተዳደራዊ መንገድ የሚያልቅ ከሆነ ተጨማሪ ቀረጥ ታክስ በማስከፈል ለእቃው መልቀቂያ መስጠት፡፡
- የተገኘው የፍተሻ ውጤት በአዋጅ 859/2006 አንቀፅ 169 መሰረት በወንጀል የሚታይ ከሆነ እቃው ሳይለቀቅ ወደ ሕግ ማስከበር ማስተላለፍ፡፡


**ፈፃሚ አካል፡- ሰነድ ምርመራ ኦፊሰር**

### 3.3.5 የፍተሻ ስራ

- ከሰነድ ምርመራ ኦፊሰር ሰነድ መረከብ
- በመመሪያ 119/2008 መሰረት ተገቢ አካላዊ ፍተሻ ማድረግ

- የፍተሻ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሰነድ ምርመራ ኦፊሰር system ማቅረብ፡፡

### 3.36 ስዕላዊ መግለጫ



## 4. የማበረታቻ ስርአት

የእቃ አወጣጥ ስርአት መፈፀምበpre- arrival clearance ፈቃደኛ ሆነው የሚስተናገዱ አስመጪዎች ቅድሚያ ቀረጥና ታክስ መክፈላቸው ለገቢ አሰባሰብ ሥራው ከሚያደርጉት አስተዋፅኦ በተጨማሪ ስርአቱ ለሚያስገኘው የተለያየ ጥቅም ማለትምፈጣን አገልገሎት እንዲኖር በማድረግ ንግድ እና ኢንቨስትመንትን ማበረታታት እንዲሁም የእቃዎችን የወደብ ላይ ቆይታእንዲያጥር በማድረግ ለሚገኘው ውጤት ትብብር እያደረጉ ስለሆነ በመደበኛ (normal procedure)ከሚስተናገዱ አስመጪዎች በተለየ መልኩ በደረቅ ወደቦች አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ቅድሚያ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

- በዚሁ መሠረት በጉምሩክ በኩል ቅድሚየ የመጋዘን ድልድል፣ቅድሚያ ፍተሻ፣ቅድሚያ የሰነድ ምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙይደረጋል፡፡
- በኢባትሎአድ በኩል ቅድሚያ እቃቸውን ለፍተሻ የማቅረብ እና መልቀቂያ ሲያገኙ ቅድሚያ የጭነት አገልግሎት እንዲያገኙይደረጋል፡፡
- በተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በኩል ፍተሻ የሚያስፈልጋቸው ገደብ የተደረገባቸው እቃዎች ቅድሚያ አገልግሎት እንዲሰጣቸው ይደረጋል

## 5. አስመጪዎች መረጃ የሚያገኙበትን ስርአት መዘርጋት

- በየእቃ አወጣጥ ስርአት መፈፀም(pre- arrival clearance) ትግበራ የተሳካ እንዲሆን ለማድረግ ጅቡቲ የደረሱ ወይም የተጫኑ እቃዎችን መረጃ አስመጪዎች በቀላሉ የሚያገኙበትን ስርአት መዘርጋት የግድ ነው፡፡ ስለሆነም ኢባትሎአድ ይህንን የመረጃ መስጫ ስርአት በመዘርጋት በpre- arrival clearance ተጠቃሚዎች መረጃ በቀላሉ የሚያኙበትን ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡

## 6. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኃላፊነት

ስርአቱ ተግባራዊ የሚደረገው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በኩል ስለሆነ ለተግባራዊነቱ ቅድሚያ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት

- ከዋናው መ/ቤት በኩል በሚላከው አሰራር መሰረት ለፈፃሚዎች ኦረቴሽን መስጠት

- በpre- arrival clearance በሚላከውየሚስተናገዱ ሰነዶች የሰነድ ምርመራቸው ከተጠናቀቀ በኃላ ትራንዚት ተጠናቆ $T_1$Validate እስኪደረግ ድረስ በጊዜያዊነት በጥንቃቄ የሚቀመጥበት ቦታ ማዘጋጀት ፡፡
- በpre- arrival clearance የሚስተናገዱ ሰነዶች ከሌሎች ሰነዶች እንዲለዩ ለማድረግም #pre- arrival clearance$የሚል ማህተም በማሰራት ሰነዶችን መለየት
- ስርአቱ የሚያስገኘውን ጥቅም በተመለከተ ለትራንዝተሮች እና ለአስመጪዎች ኦረንቴሽን መስጠት
- በpre- arrival የሚስተናገዱ አስመጪዎችን መረጃ ለይቶ መያዝ

## 7. የጉምሩክ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት

- የpre- arrival አሰራር ስርአት ቀርጸ ወደ ቅርንጫፎች ማውረድ
- ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ኦረንቴሽን መስጠት
- በECMS(Ethiopian customs management system) በpre- arrival clearance የዕቃ አወጣጥ ስርዓት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፡፡
- ለተግባራዊነቱ ቅርንጫፎችን መደገፍ
- ዕቃው ከመለቀቁ በፊት የማጓጓዣ፣የመጋዘን እና ሌሎች ክፍያዎች የተከፈለበት ስለመሆኑ ማስረጃ እንዲቀርብ መጠየቅ፤
- በስርዓቱ ለመጠቀም ዲክለር የተደረጉ ጭነቶችን መረጃ አደራጅቶ በመያዝ ዕቃዉ ወደብ ከመድረሱ በፊት ለባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ማሳወቅ፤
- በተዘረጋው ስርዓት ዲክለር ተደርገው ደረቅ ወደብ የገቡ ዕቃዎች እንደ ስጋት ደረጃቸው ፈጥነው እንዲወጡ ጥብቅ ክትትል ማድረግ
- በዚህ ስርዓት ደረቅ ወደብ የገቡ ዕቃዎችን በተቀመጠው ጊዜ ቀርበው በማያስፈትሹ፤ መልቀቂያ ተሰጥቶ ፈጥነው የማያስወጡ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ሲያጋጥሙ ተከታትሎ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፤
- አፈፃፀሙን መገምገም

8. የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ተግባርና ኃላፊነት

- በመልቲ ሞዳል ስርዓት የሚጓጓዙ ጭነቶች ከመነሻ ወደብ እንደተጫኑ ለአስመጪው በተለያዩ መንገዶች ማሳወቅ፤
- ዕቃዎች ጅቡቲ ወደብ እንደደረሱ እንዲሁም ወደ አገር ውስጥ በመጓጓዝ ላይ እያሉ በተለያዩ ዘዴዎች ለአስመጪዎች ማሳወቅ እና በአካል ቀርበው መረጃ ሲጠይቁ መረጃ መስጠት፤
- ዲክለራሲዮን ለመመዝገብ የሚያስችል የማጓጓዣ ወጪ ማስረጃ ዕቃው ከጅቡቲ ወደብ ከመነሳቱ አስቀድሞ ለአስመጪው ወይም ወኪሉ መስጠት፤
- በአርንጓዴ ወይም በቢጫ የስጋት ደረጃ የጉምሩክ መልቀቂያ ያገኙ ጭነቶች ተጓጉዘው በመጡበት ተሽከርካሪ ወደ አስመጪው መጋዘን እንዲጓጓዙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ እንዲሁም በቀይ የስጋት ደረጃ የተደለደሉ ጭነቶች ወደ ተርሚናል ሳየሄዱ በቀጥታ ወደ ፍተሻ ቦታ ማራገፍ እና ከጉምሩክ በሚሰጥ ትዕዛዝ መሰረት ለፍተሻ ዝግጁ ማድረግ፤

9. የአስመጪ ወይም ወኪል ኃላፊነት

- ግዥ የተፈፀመባቸው ዕቃዎች ከሚጫኑበት ወደብ ስለመነሳታቸው ወይም ጅቡቲ ወደብ ስለመድረሳቸው ከአጓጓዡ መረጃ መጠየቅ እና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፤
- የባንክ ግዴታን በመወጣት ዲክለራሲዮን መመዝገብ የሚያስችሉ ሰነዶችን ፈጥኖ መረከብ፤
- የማጓጓዣ ወጪ ማስረጃ /Freight Invoice/ ሰነዶች ከአጓጓዡ በመረከብ ዲክለራስዮን በመመዝገብና ቀረጥና ታክስ በመክፈል ወዲያውኑ ሰነዱን ለጉምሩክ ፌዝቤት ማስረከብ፤
- ዕቃው የተቆጣጣሪ መ/ቤት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ሲሆን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ዕቃው እንደደረሰ ፈጥኖ ማስመርመር
- ዕቃው ደረቅ ወደብ ከመድረሱ አስቀድሞ የሰነድ ምርመራ የሚከናወን ስለሆነ ከጉምሩክ ለሚቀርቡ መጠይቆች ፈጥኖ ምላሽ መስጠት፤
- ዕቃው በዝቅተኛ ወይም መካከለኛ ስጋት ደረጃ የተመደበ ከሆነ ዕቃው እንደደረሰ ትራንዚት ማኒፌስት በማዘጋት ከክሊራንስ ዩኒት የዕቃ መልቀቂያ በመረከብ ዕቃውን ፈጥኖ ማስወጣት፤ዕቃው በከፍተኛ ስጋት ደረጃ የተመደበ ከሆነ ወዲያውኑ ቀርቦ ማስፈተሽ፤